የ2017 በጀት አመት ሪፓርት
Annual Report 2024/25

ዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ.

DYNAMIC MICROFINANCE INSTITUTION S.C.

የዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም /DYNAMIC MFI/

ራዕይ

በደንበኞች ላይ ያተኮረ በሀገሪቱ ውስጥ ተመራጭ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም መሆን፡፡

ተልዕኮ

የደንበኞችን ፍላጎት በማሟላት ቀጣይነት ያለው እድገትና ትርፋማነትን ለማረጋገጥ ውጤታማ፣ ተመራጭና አስተማማኝ የሆነ የፋይናንስ አገልግሎት ማቅረብ።

ዓላማ

የዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ ዋና ዋና አላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፡፡

- በገንዘብ አቅም ራሱን ለማጠናከር ቀጣይነት ያለው ቁጠባ ከህብረተሰቡ መሰብሰብ፤
- አዋጭ በሆነ የስራ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ ነጋዴዎች፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ህጋዊ ለሆኑ ድርጅቶች፣ ለገበሬዎች እንዲሁም ለመሳሰሉት የስራ ማስጀመሪያ ወይንም ማስፋፊያ የሚሆን ብድር መስጠት፤
- ትርፋማ ከሆኑ ድርጅቶች፣ ባንኮች፣ እንዲሁም ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ቦንዶችን ወይንም አክሲዮኖችን መግዛት፤
- ለደንበኞቹ የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ውጤታማና ትርፋማ እንዲሆኑ እገዛና ድጋፍ ማድረግ፤
- ለግለሰቦችም ይሁን ለድርጅቶች የፈንድ አስተዳደር አገልግሎት መስጠት፤
- ስራ የሚያከናውንባቸውን ሕንጻዎችን ጨምሮ ማናቸውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት መግዛት፣በባለቤትነትመያዝ፣በሊዝ ማከራየት፣መንከባከብና ለሌሎች ማስተላለፍ፡፡

Vision

To be customer-centric and preferred microfinance institution in the country.

Mission

We are dedicated to providing efficient, preferred, and reliable financial services exceeding our customers' expectations while ensuring continuous growth and profitability.

Objectives

The main objectives of Dynamic Microfinance Institution are as follows: -

- To continuously collect savings from the community to strengthen its financial capacity;
- To provide loans for start-ups engaged in feasible business or particularly for expansion of existing small and medium enterprises, legal entities, and farmers;
- To purchase shares from various profitable companies, like banks, and insurance companies;
- To help and support customers so as to enable them to be effective and profitable, in their field of business engagement, by providing various trainings;
- To provide fund management services to individuals and organizations;
- To purchase any movable or immovable property including buildings used for business; to own; lease; take care of and pass the ownership rights to others.

ማውጫ

Table of Contents

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት (Board of Directors)....1

የሥራ አመራር አባላት (Executive Management)....2

የቦርድ ሰብሳቢው መልዕክት (Message from the Board Chairperson)....3

የዋና ሥራ አስፈፃሚው መልዕክት (Message from the CEO)....4

ምዕራፍ አንድ (Chapter One) 5

1.1 መግቢያ (Introduction) 5

1.2 የዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ እይታ (Overview of the Global and National Economy) 6

1.3 የፋይናንስ ኢንዱስትሪ (The Finance Industry) 6

ምዕራፍ ሁለት (Chapter Two) 8

2 . የኦፐሬሽን ስራ አፈፃፀም (Operational Performance) 8

2.1 ቁጠባን የመሰብሰብ አፈፃፀም (Saving Mobilization Performance) 8

2.2 የብድር አፈፃፀም (Loan Portfolio Performance) 9

2.3 አዲስ ቅርንጫፎችን መክፈት (New Branch Opening) 11

ምዕራፍ ሶስት (Chapter Three)....12

3. የፋይናንስ ሥራ አፈፃፀም (Financial Performance)....12

3.1 ጠቅላላ ሀብት (Total Assets) 12

3.2 ኢንቨስትመንት (Investments) 13

3.2.1 በአክሲዮን ግዢ ላይ የተደረገ ኢንቨስትመንት (Investment in Share Companies) 13

3.2.2 በሕንፃ ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት (Investment in Building) 13

3.3 እዳ (Liabilities) 14

3.4 ጠቅላላ ካፒታል (Total Equity) 15

3.5 ጠቅላላ የአክሲዮን መጠን (Total Shares) 15

3.6 ጠቅላላ ገቢ (Total Revenues) 16

3.7 ጠቅላላ ወጪ (Total Expenses) .... .17

3.8 ጠቅላላ ትርፍ (Total Profit) 18

ምዕራፍ አራት (Chapter Four) 19

4. የሰው ኃይልና ሌሎች ተግባሮች አፈጻጸም (Human Resource and Other Activities) 19

4.1 የሰው ኃይል (Human Resource) 19

4.2 የመረጃ አያያዝ አፈፃፀም (Management Information System) 19

4.3 የአጋርነት ትስስሮች (Partnership) 20

4.4 የመልካም አስተዳደር አፈፃፀምና፣ ለቦርድ ዳይሮክተሮች እና ለዋና ስራ አስፈፃሚ የተደረጉ ክፍያዎች(Corporate Governance and Remunerations to the Board of Directors and the Chief Executive Officer).. 20

4.5 ለቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራባቸው ነጥቦች(Major Focus Areas for the Coming Budget Year)....21

4.6 ለቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራባቸው ነጥቦች(Major Focus Areas for the Next Plan Period)....21

4.7 ማጠቃለያ (Conclusion) 22

የዳይሬክተሮች ቦርድ (Board of Directors)

Tesfaye Fente
Chairperson

Bekele Bayissa
D/Chairperson

Workineh Tesfaye
Director

Mengesha Dibekulu
Director

Abebaw Zewdie
Director

Yilma Gebrie
Director

Samuel Tadesse
Director

Binalfew Nega
Director

Yohannes Emiru
Director

የሥራ አመራር (Executive Management)

Bewketu Alamirew
CEO

Abiyu Tewabe
Chief Operation Officer

Amsalu Gelaneh
Chief Resource Officer

Samson Getahun
Director – Internal Audit & Risk Management

Kebede Belachew
Director – Legal Service

Message from the Board Chairperson

ተስፋዬ ፈንቴ

የተከበራችሁ ባለድርሻ አካላት፣

ኩባንያችን ከተመሰረተ 16 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ራሱን አድሶ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ባለፉት 8 ዓመታት ውስጥ በርካታ ተግባሮችን ማከናውን የቻለ ጠንካራ የፋይናንስ ተቋም ነው። በመሆኑም በእነዚህ ጊዚያት ውስጥ አቅሙ በፈቀደው መጠን ከ70 ሺህ በላይ ለሆኑ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የብድርና ቁጠባ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከ200 ላላነሱት ቋሚና ጊዚያዊ ሰራተኞች የስራ እድል ፈጥሯል።

ተቋሙ ያስቀመጠውን ራዕይ እና ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ ቁርጠኛ የሆነ አቋም ያለው እንደመሆኑ መጠን በርካታ ፈተናዎችን ቢያሳልፍም በፈተናዎቹ ሳይበገር ሁልጊዜ ለደንበኞቹ እና ለኩባንያው ዘላቂ እድገትና ልማት የሚሰራ ተቋም ነው። በዚህም ረገድ ጊዜውን የዋጁ እና ደንበኛ ተኮር የሆኑ ፈጣን የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ቁርጠኛ አቋም ያለው ተቋም ነው። ስለሆነም የማኔጅመንት እና የቦርድ አባላት ተቋሙን በሙያዊ ብቃት ለመምራት ያሳዩት ቁርጠኝነት እጅግ የላቀ ነው።

በመሆኑም በአለም አቀፍ ኢኮኖሚ ውስጥ የተከሰቱት አሉታዊ ተፅዕኖዎች በሀገሪቱ ውስጥ ከተከሰቱ ግጭቶች እና የሰላም እና የጸጥታ ችግሮች ጋር ተዳምረው በኩባንያው እድገት ላይ ተፅዕኖ ቢያሳድሩም ያጋጠሙንን እና እያጋጠሙን ያሉ ፈተናዎችንና ተግዳሮቶችን ሁሉ፣ ልምድ እና ቁርጠኝነት ባላቸው የቦርድ አባላትና እና ሰራተኞቻችን ታግዘን ግባችን ላይ ለመድረስ የተቻለውን ሁሉ እንደሚደረግ አልጠራጠርም። ቀጣይነት ያለው እድገት ለማስመዝገብ ዳይናሚክ በመልካም አስተዳደር መርሆዎች መሰረት ይሰራል።

ተቋሙ ለደንበኞቻችን ምቹ የሆኑና ሰፊ አማራጭ ያላቸው የፋይናንስ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ጠንካራ የፋይናንስ መድረክ ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት እያደረገ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ራሱን ትልቅ ቦታ ለማድረስ አልሞ የሚንቀሳቀስ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ትኩረታችንን ሁሉ በማጠናከር በሚቀጥሉት ሶስት አመታት ውስጥ የታለመውን ስኬት እና ዘላቂ እድገት እናስመዘግባለን የሚል ፅኑ እምነት አለን።

በመጨረሻም፣ ዓመቱን ሙሉ ንቁ እና ቁርጠኛ ተሳትፎ ሲያደርጉ ለነበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ የማኔጅመንት አባላትና ሰራተኞች፣ የኩባንያው ደንበኞችና ባለአክሲዮኖች፣ እንዲሁም የስራ አጋሮች ሁሉ ያለኝን ልባዊ ምስጋና መግለጽ እፈልጋለሁ።

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ!

አመሰግናለሁ!

Dear Stakeholders,

Our company has been established before 16 years ago, and it is a strong financial institution that has been able to perform many tasks in the last 8 years since it has reform itself and started working. Therefore, it has providing loan and savings services for more than 70 thousand customers as much as it can, and it has created job opportunities for more than 200 permanent and temporary employees.

As the institution is determined to achieve its vision and mission, it always working hard for the sustainable growth and development of its customers and shareholders despite many challenges. In this regard, it is a committed to providing timely and customer-oriented financial services. Therefore, the Management and Board of Directors have been making special efforts to continuously enhance our financial stability, professionalism and corporate integrity.

Although the negative effects of the global economy combined with the conflicts and peace and security problems in the country have affected the company's growth, we have no doubt that everything possible will be done to reach our goals with the help of our experienced and committed board members, management, and employees.

The institution is making great efforts to create a strong financial platform that provides convenient and wide-ranging financial services to our customers. Also, as an institution that aspires to achieve a great position in the financial sector, we believe that we will achieve the targeted success and sustainable growth in the coming years by strengthening our focus.

Finally, I would like to express my sincere gratitude to the Board of Directors, management, employees, shareholders, business partners, and customers, who have been actively and committedly involved throughout the year.

May God bless Ethiopia and its people!

Thank you!

Message From the CEO

በዕውቀቱ አላምረው

ውድ የተከበራችሁ ባለድርሻ አካላት፤

ዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ በግንቦት ወር 2001 ዓ.ም የኦፐሬሽን ስራውን አንድ ብሎ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እነሆ 16ኛ አመቱን ለማክበር የቻለ አንጋፋ ተቋም ነው። ተቋማችን ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ችግሮችና መሰናክሎች የነበሩበት ቢሆንም አዳዲስ ባለራዕይ ባለአክሲዮኖች ወደ ተቋሙ በመቀላቀልና በሁሉም የስራ ዘርፎች በየዓመቱ እድገት በማስመዝገብ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የተቋሙ በርካታ ቅርንጫፎች በሚገኙበት በአማራ ክልል ውስጥ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ጋር በተያያዘ በተቋሙ አጠቃላይ የስራ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮ የነበረ ቢሆንም እንደተቋም ቸግሮችን ሁሉ እንደ እድል በመውሰድና በየጊዜው የሚፈጠረውን ስጋት ለመቀነስ በርካታ ማስተካከያዎችን ማድረግ ተችሏል።

ተቋሙ በእነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት ሁሉ በችግሮች ሳይበገር የተቋሙን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ስልቶችን ተግባራዊ አድርጓል። ይህም ከቅርንጫፎቹ ጋር ያለውን የግንኙነት መንገዶችን ማጠናከር፣ የመረጃ አያያዝ ስርዓትን ማሻሻል፣ የገንዘብ አስተዳድር ስርዓትን ማዘመን፣ እና የፋይናንስ አገልግሎት አማራጮችን ማብዛትን የሚያካትት ሲሆን ለዚህም የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ የማኔጅመንት አባላትና ሰራተኞች አመቱን ሙሉ በጥምረት ለሰሯቸው በርካታ ችግር ፈቺ ስራዎች ሊመሰገኑ ይገባል።

በመጨረሻም አክሲዮን ማኀበሩ በሚያከናውናቸው ተግባሮች ሁሉ ድጋፍና እገዛ ስታደርጉልን ለነበራችሁ ባለአክሲዮኖች፣ ጠንክራችሁ ስትሠሩ ለነበራችሁ የቦርድና የማኔጅመንት አባላት እና ሠራተኞች፣ ለደንበኞቻችን፣ እንዲሁም ለአጋሮቻችን ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና እያቀረብኩ በ2018 በጀት ዓመት ሀገራችን ውስጥ ሰላም ሰፍኖ የተቋሙን ሕልውናና ውጤታማነት ከዚህ በበለጠ የምናስቀጥልበት ዘመን እንዲሆንልን መልካም ምኞቴን እገልፃለሁ፡፡

ፈጣሪ አገራችንንና ህዝባችንን ይባርክ።

አመሰግናለሁ።

Dear Stakeholders,

Dynamic Microfinance Institution is a veteran institution that has been able to celebrate its 16th anniversary since it started its operations in May 2009. Since the establishment of our institution, there have been many problems and obstacles, but new visionary shareholders have joined the institution and it has been able to reach its current level by achieving progress in all areas of work every year.

In the past two years, the security crisis in the Amhara region, where many branches of the institution are located, had a negative impact on the overall performance of the institution, but as an institution, it was possible to take the problems as an opportunity and make several adjustments to reduce all the threats that arise from time to time.

Dynamic has implemented various strategies to ensure the continuity of the institution during these difficult times. This includes strengthening the communication channels with the branches, improving the information management system, increasing the financial service options.

Finally, I would like to express my sincere gratitude to the shareholders who have been supporting and helping us in all the activities and to the Board of Directors, management members, and employees who have been working hard, as well as to all our partners.

May God bless our country and people!

Thank you.

ምዕራፍ አንድ

1.1 መግቢያ

ዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ. በመላው ሀገሪቱ ውስጥ መስራት የሚያስችለውን የሥራ ፈቃድ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በማግኘት ከግንቦት 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በአዲስ አበባ እንዲሁም በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ቅርንጫፎችን ከፍቶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ተቋሙ አሁን ያለበት የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ በርካታ መሰናክሎችን ማለፉ የሚታወስ ነው፡፡ በመሆኑም ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮችን በመመርመር ተቋማዊ ሪፎርም ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ በተለይም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በርካታ ተግባሮችን ማከናወን ችሏል። በዚሁ መሰረት ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ራሱን በካፒታልና በሰው ኃይል በሚገባ አደራጅቶ ወደ ተግባር በመግባት በቢሮ አደረጃጀት፣ በብድር ስርጭት፣ በብድር አመላለስ እና በቁጠባ አሰባሰብ ተግባር ላይ በየጊዜው የሚያጋጥሙ ፈታኝ የሆኑ ችግሮችን ሁሉ በማለፍ የተቋሙን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በየዓመቱ በርካታ ተግባሮችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የተቋሙ በርካታ ቅርንጫፎች በሚገኙበት በአማራ ክልል ውስጥ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ጋር በተያያዘ በተቋሙ አጠቃላይ የስራ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሮ የነበረ ቢሆንም እንደተቋም ችግሮችን እንደ እድል በመውሰድና በየጊዜው የሚፈጠረውን ስጋት ለመቀነስ በርካታ ማስተካከያዎችን ማድረግ ተችሏል።

በዚሁ መሰረት የተፈጠረውን ችግር ለመቋቋም ተገቢ የሆነ እስትራቴጂ በመንደፍ የተቋሙን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን በተለይም ተቋሙ የገንዘብ እጥረት እንዳይገጥመው ብድር በወቅቱ እንዲመለስና ከህብረተሰቡ ቁጠባ በስፋት እንዲሰበሰብ ለማድረግ ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል። በመሆኑም በብድርና በቁጠባ አሰባሰብ ስራ ላይ የተሻለ ውጤት በማስመዝገብ የደንበኞችን የቁጠባ ወጪ፣ የባንኮችን የብድር ክፍያ፣ የሰራተኞች የደመወዝ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎችን ያለችግር መክፈል ተችሏል። ስለሆነም የኩባንያውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ቦርዱ ስራውን በከፍተኛ ሁኔታ ለመከታተል በመደበኛነት በየወሩና በየሩብ ዓመቱ ቋሚ ስብሰባዎችን እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በርካታ አስቸኳይ ስብሰባዎችን አካሂዷል፡፡

Chapter One

1.1 Introduction

May 2009 marked the birth of Dynamic Microfinance Institution (DMFI) as a share company, meeting the requirements of Proclamation No. 626/2009 and the National Bank of Ethiopia's relevant directives. Since its establishment, DMFI has been able to open and run 28 branch offices in Addis Ababa, Oromia, and Amhara Regions.

DMFI has been making its own contribution in filling the gap between the demand and supply of financial services thereby placing its footprint in the development of the country. The institution has recognized that there are certain parts of the society in the economy that are not addressed well by the formal financial sectors but play a significant role in the well-being of the community.

Therefore, in the past two years, the security crisis in the Amhara region, where many branches of the institution are located, had a negative impact on the overall work performance of the institution, but as an institution, it was possible to take the problems as an opportunity and make several adjustments to reduce the threat that arises from time to time.

It was possible to ensure the continuity of the institution by designing an appropriate strategy to deal with the problem, especially to ensure that the loans given to the borrowers are returned on time, as well as to collect savings from the society. As a result, it has been able to pay customers' savings costs, bank loan payments, employees' salary payments and other payments without any problems by achieving relatively better results in the loan and savings collection work. Therefore, in order to ensure the continuity of the company, the board has regularly held monthly and quarterly standing meetings as well as several emergency meetings as needed to closely monitor its operations.

1.2 አጠቃላይ የዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ የኢኮኖሚ እይታ

ባለፉት አምስት ዓመታት በአጠቃላይ በኢኮኖሚው ዘርፍ ላይ የተለያዩ ተግዳሮቶችን የፈጠሩ የተለያዩ ዓለም አቀፋዊ እና አገር አቀፍ ክስተቶች ተስተውለዋል። ይኸውም በዋናነት በተለያዩ ሀገራት በሚፈጠሩ ጦርነቶች ምክንያት ለማቴሪያል አቅርቦት ሰንሰለት መስተጓጎል እና ለሸቀጦች ዋጋ መናር መንስዔ በመሆን በአለም ኢኮኖሚ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ይህ በመሆኑም የዋጋ ግሽበቱ የብዙ ሃገራት ብሔራዊ ባንኮች ከገመቱት በላይ በመሆኑ የገንዘብ ፖሊሲዎቻቸውን ለማጥበቅ አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሯል።

በአለም አቀፍ ኢኮኖሚው ላይ እንደተስተዋለው ሁሉ የኢትዮጵያም ኢኮኖሚ በተለይም ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ በርካታ ተግዳሮቶችን አስተናግዷል። በዋነኝነት በፀጥታ ችግር፣ በተለይም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍሎች በተከሰተው ጦርነት፣ የዶላር በብር ምንዛሬ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር፣ እንዲሁም በፋይናንስ ሴክተር ላይ በተሰራው የሪፎርም ምክንያቶች በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

በመሆኑም ከማዕከላዊ ስታስቲክስ ኢጀንሲ ሪፖርት ላይ ለመረዳት እንደሚቻለው የአገር አቀፍ አጠቃላይ የሸቀጥ ዋጋ ላይ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የሆነ ጭማሪ አሳይቷል።

1.3 የፋይናንስ ኢንዱስትሪን በተመለከተ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቆጣጠራቸው በሀገራችን ውስጥ ያሉ የመንግስትና የግል የፋይናንስ ተቋማት በርካታ ናቸው። እነሱም ባንኮች፤ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፤ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፤ እና የሊዝ ፋይናንስ ኩባንያዎች ዋናዎቹ ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት ለህበረተሰቡ የተሟላ የፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት ብዛታቸው 32 ባንኮች፤ 18 የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፤ ከ60 በላይ የሆኑ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፤ 21 የፋይናንሺያል ተክኖሎጂ ኩባንያዎች (FinTech) ፤ 13 የውጭ ምንዛሬ ቢሮዎች፤ 89 የገንዘብ ማስተላለፊያ ወኪሎች፤ እና 6 የሊዝ ፋይናንስ ኩባንያዎች ናቸው፡፡

1.2 Overview of the Global and National Economy

Various global and national events have been unfolding in the past five years that have created various challenges for the economy as a whole. Among the major ones, wars and conflicts in different parts of the world not only disrupted the material supply chain but also resulted in increased commodity prices, which had a significant negative impact on the world economy. As a result, inflation has once again surpassed forecasts and compelled national banks in numerous nations to tighten their monetary policies.

Like the international economy, Ethiopia's economy has also faced many challenges, especially in the last three years. Ethiopia's economy has been adversely affected, mainly due to the instability in the northern parts of the country.

The Central Statistics Agency study states that the national commodity price has increased as compared to the previous year.

1.3 Overview of the Global and National Economy

The National Bank of Ethiopia regulates a large number of state and private financial organizations. These include banks, insurance providers, microfinance organizations, and lease finance firms that presently offer the community official financial services. In Ethiopia, there are currently 32 banks, 18 insurance companies, over 60 microfinance organizations, 10 payment instrument issuers, 21 fintech, and 1 Reinsurance company .

በመሆኑም በአገራችን በፋይናንስ ኢንዱስትሪ ውስጥ በሀብት ማሰባሰብ እንዲሁም ደንበኛ በማፍራት ስራ ላይ ያለው ውድድር እና ፉክክር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። ውድድሩ በባንኮች፤ በማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ በፋይናንሺያል ተክኖሎጂ ኩባንያዎች (FinTech) እንዲሁም በክፍያ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል መሆኑ ደግሞ የደንበኞችን አገልግሎት ለማሻሻል መንስዔ ከመሆኑም በላይ በገበያው ላይ ያለውን ፉክክር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ይገኛል። ይህንንም ተከትሎ በአብዛኛው የፋይናንስ ተቋማት ጥራት ያለው አገልግሎት ለደንበኞቻቸው ለማዳረስ ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ዲጂታል ተኮር የሆኑ የፋይናንስ አገልግሎቶችን መስጠት ላይ አተኩረው በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ባላቸው የቅርንጫፎች ብዛት፤ በአገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት፤ በሀብት መጠን፤ እና በካፒታል መጠን የእድገት ደረጃቸው ትልልቅ፤ መካከለኛና ዝቅተኛ ተብለው ተመድበው ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ኩባንያችን ከላይ በተገለፁት መመዘኛዎች መሰረት በአሁኑ ወቅት በመካከለኛ ደረጃ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ወደ ትልቅ ደረጃ ለመሸጋገር አሁን ያለውን የሀብትና የካፒታል መጠን ለማሳደግ በቀጣይ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ብዙ ይጠበቃል፡፡

The level of rivalry between financial organizations to recruit customers and mobilize financial resources is occasionally getting more intense. Financial institutions are being forced to use cutting-edge modern technologies to improve customer service quality due to competition from banks, MFIs, financial technology (Fintech) companies, and issuers of payment instruments.

Based on the number of branches, total assets, capital, and customers, microfinance institutions are categorized as large, medium, or small by the National Bank of Ethiopia. This classification places DMFI in the medium class at the moment, and it is making a concerted effort to fortify and expand its capital and assets in order to advance to the next higher level. All parties involved are required to continue and improve their support in this area.

ምዕራፍ ሁለት

2. የኦፐሬሽን ስራ አፈፃፀም

2.1 ቁጠባን የመሰብሰብ አፈፃፀም

የተቋሙን የገንዘብ አቅም ለማጠናከር እና ለህብረተሰቡ የብድር አገልግሎት በስፋት ለማዳረስ ከብድር ደንበኞችና የብድር ደንበኛ ካልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መጠነ ሰፊ የሆነ ቁጠባ መሰብሰብ የዘወትር ተግባር ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የገጠሙንን ፈተናዎች ሁሉ በመቋቋም በበጀት ዓመቱ ማኔጅመንቱና ሰራተኛው ቁጠባ በስፋት ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ከመቼውም የተሻለ ውጤት ተመዝግቧል።

በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ለመድረስ የታቀደው አጠቃላይ የቁጠባ መጠን 368,915,000 ብር ሲሆን በዓመቱ አፈፃፀም 346,542,406 ብር መድረስ ተችሏል፡፡ ይህም የዓመቱ እቅድ ከንውን አፈፃፀምን በ94% ማሳካት እንደተቻለ ያሳያል፡፡ ይህ አፈፃፀም ባለፈው በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከነበረው ጠቅላላ የቁጠባ መጠን ከብር 205,449,257 ጋር ሲነፃፀር በ141,093,149 ብር ብልጫ ወይንም የ69% እድገት እንዳለው ያሳያል፡፡

ይህ እንዲሆን በበጀት ዓመቱ በየደረጃው ባለው በሁሉም አካል ለቁጠባ ልዩ ትኩረት በመስጠት ለመስራት ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ በሁሉም ቅርንጫፎች የቁጣባ ሂሳብ በብዛት በማስከፈት እና በመጠኑ የተሻለ ቁጠባ በማስቆጠብ ረገድ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ በቁጠባ አሰባሰብ ላይ ያስመዘገበውን እድገት ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

Chapter Two

2. Operational Performance

2.1 Saving Mobilization Performance

Large-scale savings from loan and non-loan clients must be mobilized in order to expand the institution's financial capacity and provide credit services to the general public. As a result, the management and staff have worked hard to encourage better savings during the budget year.

The total amount of savings planned to reach at the end of the 2024/25 fiscal year is 368,915,000 Birr and the performance of the year has reached 346,542,406 Birr. This shows that the implementation of the plan for the year has been achieved by 94%. This performance shows an increase of 141,093,149 Birr or 69% growth compared to the total savings amount of 205,449,257 Birr at the end of 2023/24 fiscal year.

In order for this to happen, great efforts have been made to work by paying special attention to savings in all levels of the fiscal year. In all branches, it was possible to achieve better results in terms of opening more accounts and saving slightly better.

The graph below illustrates the growth in savings balances during the previous five years.

ምስል 1፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የቁጠባ እድገት



2.2 የብድር አፈፃፀም

ከቁጠባ አገልግሎት ቀጥሎ የፋይናንስ ተቋማት ለተጠቃሚው ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች አንዱ የብድር አገልግሎት ነው፡፡ በመሆኑም ጥራት ያለው የብድር አገልግሎት ለህብረተሰቡ በስፋት መስጠት ከብድር የሚገኘውን የተቋሙን የገቢ ምንጭ ከማሳደጉም በላይ ተጨማሪ ቁጠባን ለመሰብሰብ በር ከፋች መንገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በፋይናንስ ዘርፉ ላይ የተፈጠረው ችግር የብድር አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ እንዲሁም በብድር ስርጭት፣ በብድር አሰባሰብ፣ እና በተበዳሪዎች እጅ ላይ የሚኖረውን የብድር መጠን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮ አልፏል።

በመሆኑም የበጀት ዓመቱ የብድር ስራ እቅድ ክንውን አፈፃፀምና የተገኘው ውጤት ካለፈው ተመሳሳይ የበጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር እንደሚከተለው ነው፡፡

1) በበጀት ዓመቱ ጠቅላላ ሊሰጥ የታቀደው የብድር መጠን 944,079,000 ብር ሲሆን የተሰጠው የብድር መጠን ሲታይ ብር 278,119,040 ብቻ ነው። ይህም በበጀት ዓመቱ ማሳካት የተቻለው የእቅዱን 29% ብቻ ሲሆን ካለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት ከተሰጠው የብድር መጠን ከብር 150,475,100 ጋር ሲነፃፀር የብር 127,643,940 ብር ብልጫ አለው።
2) በበጀት ዓመቱ ጠቅላላ ሊሰበሰብ የታቀደው የብድር መጠን ብር 728,989,000 የነበረ ቢሆንም የተሰበሰበው የብድር መጠን ግን ብር 248,024,561 ነው። ይህም በበጀት ዓመቱ ማሳካት የተቻለው የእቅዱን 34% ሲሆን ባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት ከተሰበሰበው የብድር መጠን ከብር 151,234,598 ጋር ሲነፃፀር በብር 96,789,963 ብልጫ አለው።
3) በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በተበዳሪዎች እጅ ይኖራል ተብሎ የታቀደው የብድር መጠን ብር 543,842,432 ሲሆን ክንውኑ ብር 363,859,738 ነው፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ማሳካት የተቻለው የእቅዱን 67% ሲሆን ባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረው የብድር መጠን ከብር 328,752,432 ጋር ሲነፃፀር በብር 35,107,306 ብልጫ አለው፡፡

2.2 Loan Portfolio Performance

DMFI offer its clients credit services in addition to saving mobilization. As a result, offering the community high-quality credit services not only expands the institution's loan revenue stream but also opens up a saving opportunity. In order to improve access to credit services, loan disbursement, loan collection, and the total amount of outstanding loans, sufficient efforts were made during the budget year.

The performance problem seen in loan distribution and transport was mainly due to the breach of peace in the Amhara region, where the majority of our institution's branches are located at the time, and this problem caused a clearly visible negative effect on the overall performance of the institution.

1) The total loan amount planned to be disbursed during the budget year was Birr 944,079,000 and the actual amount of loan granted was Birr 278,119,040. This implies an achievement of 29% of the plan. Compared to the loan amount of Birr 150,475,100 granted in the previous year, it represents an increase of Birr 127,643,940.
2) Likewise, the total amount of loan planned to be collected from borrowers was Birr 728,989,000; whereas the actual amount collected was Birr 248,024,561. This implies an achievement of 34% of the plan. Compared to the loan amount collected in the previous year, i.e., Birr 151,234,598, it represents an increase of Birr 96,789,963.

4) በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ከ90 ቀን በላይ ሳይከፈል የቆየ የተበላሸ የብድር መጠን ከላይ በተገለፁት ችግሮች ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ የነበረ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ በተደረገው ከፍተኛ ርብርብ ባለፈው ዓመት ከነበረው የተበላሸ የብድር መጠን ከብር 119,625,54 ወደ ብር 96,137,267 ማውረድ ተችሏል። ይህም ባለፈው ተመሳሳይ የበጀት ዓመት ላይ ከነበረው የተበላሸ የብድር ምጣኔ ከ36% ጋር ሲነፃፀር በበጀት ዓመቱ ወደ 26% ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከላይ በመግቢያው ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በብድር ስርጭትና አመላለስ ላይ የታየው የአፈፃፀም ችግር በዋናነት በወቅቱ አብላጫ ቁጥር ያላቸው የተቋማችን ቅርንጫፎች በሚገኙበት በአማራ ክልል ውስጥ በተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ምክንያት ሲሆን ይህ ችግር ደግሞ በተቋሙ አጠቃላይ የስራ አፈፃፀም ላይ በግልፅ የሚታይ አሉታዊ ችግር አሳድሯል።

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አ/ማህበሩ በብድር ስራ ላይ ያስመዘገበውን ውጤት ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

ምስል 2፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የብድር እድገት

3) At the end of the 2023/24 Budget Year, the planned amount of loans outstanding was Birr 543,842,432, whereas the actual amount of loans outstanding was Birr 363,859,738. This implies an achievement of 67% of the plan. As compared to the outstanding loan amount of Birr 328,752,432 achieved at the end of the last budget year, it represents an increase of 35,107,306.

4) At the end of the Budget Year, the amount of Non-Performing Loans (NPL) that had been overdue by more than 90 days has decreased from 119,625,54 to Birr 96,137,267 by improving the institution's PAR from 36% to 26%.

As previously mentioned, the peace and security issues in the Amhara region, where the bulk of DMFI's branches are located, had a huge impact on loan disbursement, collection, and outstanding portfolio.



2.3 አዲስ ቅርንጫፎችን ስለመክፈት

ቅርንጫፎች ተቋሙንና የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ተጠቀሚዎችን አገናኝ ድልድይ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ኩባንያው የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋት በየጊዜው የአዋጪነት ጥናት በማድረግ የቅርንጫፎችን ቁጥር የማሳደግ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ሆኖም በወቅቱ ከተፈጠረው ችግር ጋር ተያይዞ በበጀት ዓመቱ ተጨማሪ ቅርንጫፎች ያልተከፈቱ ሲሆን፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ተቋሙ በአጠቃላይ በ28 ቅርንጫፎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

2.3 New Branch Opening

Branches are bridges that connect the institution to its esteemed credit and saving customers. Therefore, in order to increase the institution's market outreach and improve the accessibility of financial services; it continually conducts feasibility studies and makes decisions to open additional branch offices.

However, during the budget year 2024/25, there were no additional branches opened due to the challenges faced and strategic moves taken afterward which makes the total number of operational branches 28.

ምዕራፍ ሶስት

3. የፋይናንስ ሥራ አፈፃፀም

3.1 ጠቅላላ ሀብት

ባለፉት አምስት ዓመታት ኩባንያው አጠቃላይ ያለው የሀብት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት በማደግ ላይ የነበረ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የተቋሙን አጠቃላይ የሀብት መጠን ብር 778,406,583 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ክንውኑ ደግሞ ብር 591,530,466 ሆኗል፡፡ በመሆኑም የበጀት ዓመቱ አፈፃፀም ሲታይ ተቋሙ የእቅዱን 76% ማሳከት መቻሉን ያሳያል፡፡ እንዲሁም የ2017 በጀት ዓመት አፈፃፀም ካለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረው የሀብት መጠን ማለትም ብር 517,664,225 ጋር ሲነፃፀር፤ የተገኘው እድገት የብር 73,869,241 ብር መሆኑን ለማየት ይቻላል።

ኩባንያው አጠቃላይ ካለው ሀብት ውስጥም፤ የ62 በመቶ ድርሻን የሚይዘው ከብድር የሚሰበሰብ ሀብት በመሆኑ ገቢ ሊያስገኝ የሚችል የሀብት መጠን አሁንም ከፍተኛውን ድርሻን እንደያዘ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ በአጠቃላይ ያስመዘገበውን የሀብት እድገት ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

Chapter Three

3.Financial Performance

3.1 Total Assets

The company's assets have been growing rapidly as can be manifested in the growth of fixed assets, Liability, and capital. At the end of the 2024/25 budget year, it was planned to increase the company's assets to Birr 778,406,583. However, the actual performance reached is Birr 591,530,466 and this represents 76% achievement of the plan. Compared to the previous year's attainment of Birr 501,977,914, there is an incremental change of Birr 73,869,241.

Sixty-two percent (62%) of the company's total assets belong to outstanding loans. This indicates that the highest portion of total assets is committed to the income-generating loan portfolio.

Growth of the company's assets, during the last five years, is presented on the graph below.

ምስል 3፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የሀብት መጠን



3.2 ኢንቨስትመንት

3.2.1 በአክሲዮን ግዢ ላይ የተደረገ ኢንቨስትመንት

አክሲዮን ማህበሩ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ያለውን ትስስር በማስፋት፤ በኢኮኖሚ የተሻለ ጥቅም ሊያስገኙ ከሚችሉ የፋይናንስ ኩባንያዎች ላይ አክሲዮን በመግዛት የኢንቨስትመንት አድማሱን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማስፋት ላይ ይገኛል። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በሌሎች ተቋማት ላይ ያለው የኢንቨስትመንት መጠን በድምሩ ብር 16,041,100 ደርሷል። በዚሁ መሰረት ተቋሙ የአክሲዮን ባለቤት የሆነባቸውን ተቋማትና የአክሲዮን መጠን ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

3.2 Investments

3.2.1 Investment in Share Companies

DMFI is expanding its investment scope by building partnerships with and purchasing shares of other financial institutions which are believed to bring better returns. Accordingly, the amount of investment made at these institutions during the 2024/25 fiscal year has reached a total of Birr 16,041,100. The names of the financial institutions in which the investments are made and the amount invested are disclosed in the table below.

ምስል 4፡ በበጀት ዓመቱ በተቋማት ላይ ያለው የኢንቨስትመንት መጠን



3.2.2 በሕንፃ ላይ የተደረገው ኢንቨስትመንት

በየአካባቢው ያለው የቢሮ ኪራይ ወጪ በየጊዜው በከፍተኛ ፍጥነት ከእጥፍ በላይ እየጨመረ እንደሆነ የሚታወቅ ሀቅ ነው። ስለሆነም በተቻለን አቅም ለኩባንያችን ቢያንስ በትልልቅ ከተሞች ውስጥ የራሱ ሕንፃ ወይም ቢሮ እንዲኖረው ለማድረግ አሁን ላይ የተጀመረው እንቅስቃሴ አንዱ ማሳያ ነው። ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ፤ ከዚህ በፊት ኩባንያችን የራሱ የዋና መስሪያ ቤት ሕንፃ እንዲኖረው በመደረጉ በከፍተኛ ሁኔታ ሊወጣ የሚችለውን የዋና መስሪያ ቤት የቢሮ ኪራይ ወጪ ከማዳኑም በላይ ትርፍ የሆኑ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ክፍሎችን ለባንክ በማከራየት በየወሩ ከግብር በፊት 242,433 ብር የኪራይ ገቢ ማግኘት ተችሏል። በተጨማሪም ሕንፃውን በዋስትና በማስያዝ ከባንክ ብድር በመውሰድ ለኦፐሬሽን ስራ ማስፋፊያ እንዲውል ተደርጓል። ከላይ ከተገለፁት ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በተጨማሪም ተቋሙ የራሱ የሆነ የዋና መስሪያ ቤት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ በርካታ የፋይናንስ ተቋማት ዋና መስሪያ ቤቶች በቅርብ ርቀት በመሀል ልደታ እንዲኖረው በመደረጉ በገፅታ ግንባታ፥ ራሱን በቀላሉ በማስተዋወቅ፥ እንዲሁም ደምበኞችን ጨምሮ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ዘንድ ተቋሙ ከፍተኛ የሆነ አመኔታንና ከበሬታን እንዲያገኝ አስችሎታል።

3.2.2 Investment in Building

It is a well-known fact that in every city the cost of office rent is increasing at a rapid rate. Therefore, as far as possible, due attention is given to the acquisition and ownership of its own office buildings in at least major city areas across the country. As part of the implementation of this strategic objective, acquiring the head office building contributed significantly not only by avoiding the rental expense incurred but also by creating the opportunity to earn gross rental income of Birr 242,433 per month before tax; through leasing extra floors to banks.   Moreover, by mortgaging the building as collateral, the company has been able to take commercial loans for the purpose of operational expansion. In addition to the above financial benefit, having a head office building at the heart of the country's financial hub which is also close to the National Bank of Ethiopia not only boosted DMFI's image-building endeavors but also enhanced its reputation and credibility in the eyes of customers and various stakeholders.

ይህም በአጠቃላይ እስካሁን በሕንፃ ግዢና እድሳት ላይ ኢንቨስት የተደረገውን የገንዘብ መጠን ብር 64,494,887 ሲሆን፤ ሕንፃው እያበረከተ ካለው ዘርፈ ብዙ አገልግሎት እና ከሚያስገኘው ገቢ ጋር ሲነፃፀር ኢንቨስትመንቱ በአንፃራዊነት አነስተኛ በመሆኑ ኩባንያው ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆነ በቀላሉ ለማየት ይቻላል።

3.3 እዳ

ኩባንያው በእዳ የሚያገኛቸው የገንዘብ ምንጮች በዋነኝነት የሚሸፈኑት በየጊዜው በቁጠባ ከሚሰበሰብ ገንዘብና ከባንኮች ከሚገኙ ብድሮች ነው፡፡ በመሆኑም ኩባንያው ያለበት እዳ በአብላጫዉ የሚይዙት፤ የኦፕሬሽን ስራን ለማስፋፋት እንዲረዳው በተለያየ ጊዜ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ ከአቢሲኒያ ባንክ፣ ከኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ፣ ከአዋሽ ባንክ፣ እና ከቡና ባንክ የወሰዳቸው ብድሮች እንዲሁም ከህብረተሰቡ ከቁጠባ የሰበሰበው ገንዘብ ነው። በዚህም መሰረት በ2017 በጀት ዓመት ተቋሙ በአጠቃላይ የሚኖረውን የእዳ መጠን ብር 493,388,357 ለማድረስ አቅዶ የነበረ ሲሆን፤ ከንውኑን ብር 473,166,850 ብር ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ የእቅዱን 96% አፈፃፀም ማሳከት መቻሉን ያሳያል፡፡ ይህ አፈፃፀም ካለፈው ተመሳሳይ የበጀት ዓመት ላይ ከነበረው የእዳ መጠን ብር 400,338,416 ጋር ሲነፃፀር የ72,828,416 ብር ብልጫ አለው፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ የሰበሰበውን የእዳ መጠን እድገት ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

ምስል 5፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የእዳ መጠን

The amount of money invested for the purchase and renovation of the building is Birr 64,494,887. Given the double functions the building serves, the investment amount is low even without considering the extra income it generates. This makes the company's move a synergistic happenstance.

3.3 Liabilities

In order to expand its operation's scope, the company has taken loans from the Development Bank of Ethiopia, Bank of Abyssinia, Oromia Cooperative Bank, Awash Bank, and Buna Bank. Apart from the loans obtained from these banks, the savings deposits mobilized during the budget year were significantly better than any time before. As a result, the debt of the institution has slightly increased.

During the 2024/25 budget year, it was planned to increase the size of the company's liabilities to Birr 493,388,357. The achieved performance has reached to Birr 473,166,850 and it represents the 96% achievement of the budget year plan. Compared to the total liabilities attained in the previous budget year, Birr 400,338,416, the current year performance registers an increase of Birr 72,828,416.

The growth of total liabilities of the company during the last five years is shown on the graph presented below.

3.4 ጠቅላላ ካፒታል

የኩባንያው ለአንድ ግለሰብ የማበደር አቅም የሚወሰነው ኩባንያው በወቅቱ ባለው የካፒታል መጠን እንደሆነ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ላይ በግልፅ ተደንግጓል። ስለሆነም ቦርዱ የኩባንያ ካፒታል ለማሳደግ የተለያዩ እስትራቴጂዎችን ቀርፆ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም ባለፉት ሁለት ዓመታት የተፈጠረው ችግር በካፒታል አሰባሰብ ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮ አልፏል። በዚሁ መሰረት በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የአክሲዮን ማህበሩን ጠቅላላ የካፒታል መጠን ብር 285,018,226 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በአፈፃፀም ደረጃ ሲታይ በብር 118,363,616 ወይንም የእቅዱን 42% መፈፀም ተችሏል፡፡ ይህም በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከነበረው ጠቅላላ የካፒታል መጠን ከብር 117,325,809 ጋር ሲነፃፀር የበጀት ዓመቱ አፈፃፀም በ10,387,807 ብር ብቻ ጨምሮ ይታያል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ በጠቅላላ የካፒታል መጠን ያስመዘገበውን እድገት ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

3.4 Total Equity

The single borrower limit which determines the amount of borrowing that can be taken by an individual is directly determined by that institution's capital structure. In line with this, the board has been devising and working on various capital-raising strategies. At the end of the 2024/25 budget year, it was planned to increase the total capital of the company to Birr 285,018,226. However, the actual capital registered at the year-end was Birr 118,363,616, which represents a performance of only 61%. As compared to the total capital amount of Birr 117,325,809 registered at the end of the last budget year, it shows an increase of Birr 10,387,807.

The capital growth of the company during the last five years is presented in the graph below.

ምስል 6፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የካፒታል መጠን



3.5 የተከፈለ የካፒታል መጠን

በታህሳስ 2016 ዓ.ም. በተካሄደው 6ኛው አስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በፀደቀው መሰረት የኩባንያው አጠቃላይ የካፒታል መጠን ወደ ብር 500 ሚሊዮን እንዲያድግ መወሰኑ ይታወሳል፡፡ ሆኖም እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ጠቅላላ የተፈረመው የካፒታል መጠን ብር 158,913,000 ብቻ ሲሆን የተከፈለ ጠቅላላ የካፒታል መጠንም ብር 150,122,000 ነው፡፡ በመሆኑም እስካሁን ያልተፈረመ ጠቅላላ የካፒታል መጠን በዋጋ ብር 341,087,000 ነው፡፡ ስለሆነም የኩባንያውን ቀጣይነት ይበልጥ ለማረጋገጥ ባለአክሲዮኖች የተመደበላቸውን አክሲዮን በመፈረምና በመክፈል ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ አሁንም ቦርዱ ጥሪውን ያቀርባል።

3.5 Paid Up Capital

It is to be recalled that the total value of paid up capital of the company approved at the 6th extraordinary general meeting held in December 2023 was Birr 500 million. Out of this, the total value of subscribed and paid-up capitals, till the end of the budget year, was Birr 158,913,000 and Birr 150,122,000. Therefore, it can be seen that the total value of approved capital not yet subscribed is Birr 341,087,000. Hence, in order to meet the current challenges and ensure DMFI's growth and sustainability in the industry, it requires the commitment of all shareholders to subscribe and pay the allotted amount of shares to respective shareholders.

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ በጠቅላላ የካፒታል መጠን ያስመዘገበውን እድገት ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

ምስል 7፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የተከፈለ ካፒታል መጠን

The graph below shows the growth of paid-up capital the company attained during the last five years.

3.6 ገቢ

ዳይናሚክ የፋይናንስ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የአክሲዮን ማህበሩ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ከብድር የሚሰበሰብ ወለድ ሲሆን ተጨማሪ የገቢ ምንጮች የአገልግሎት ክፍያ፣ ከቁጠባ የሚገኝ ወለድ፣ እንዲሁም ከሕንፃ ኪራይ የሚገኝ ገቢ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: በዚህም መሰረት ኩባንያው በበጀት ዓመቱ የሚሰበስበውን የገቢ መጠን በሰፊው አቅዶ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ባላፈው በጀት ዓመት ከተፈጠረው ችግር ልምድ በመውሰድ የሰላም ችግር የሌለባቸውን አካባቢዎች በመምረጥና ሙሉ ትኩረት በማድረግ ሰራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ጠቅላላ የገቢ መጠን ብር 171,352,351 ሲሆን ይህም በበጀት ዓመት ውስጥ ለመሰብሰብ ከታቀደው የገቢ መጠን ብር 181,690,768 ጋር ሲነፃፀር ክንውኑ 94% ነው:: በዚህ በጀት ዓመት የተሰበሰበው የገቢ መጠን ባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት ከተሰበሰበው የገቢ መጠን ከብር 80,562,467 ጋር ሲነፃፀር የ90,789,884 ብር ብቻ ብልጫ ወይንም የ113% እድገት አለው::

በመሆኑም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ በገቢ አሰባሰብ ላይ ያስመዘገበውን እድገት ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

3.6 Total Income

During the concluded budget year, DMFI planned various activities, especially pertaining to the enhancement of resource mobilization, loan disbursement, loan collection, and maintaining a healthy loan portfolio.

As a financial institution, the company's main source of revenue is interest collected from loans. Additional sources of income include service fees, loan insurance, interest from savings, and others. The above main two sources of income were seriously hampered by the peace and security issues faced in the Amhara region. Hence, it is worth noting that the below-registered result shows DMFI's performance mainly with only 11 branches found in Addis Ababa and Oromia region.

The total income collected during the 2024/25 budget year was Birr 171,352,351, and this represents 94% of the planned revenue of Birr 181,690,768. Compared to the income of Birr 80,562,467 generated the previous budget year, there is an increase of Birr 90,789,884.

Graph shown below depicts the annual amount of income the company generated during the last five years.

ምስል 8፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የገቢ መጠን



3.7 ወጪ

ኩባንያው በተቻለ መጠን ወጪ ቆጣቢ የሆነ አሰራር ዘርግቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። በ2017 በጀት ዓመት ለሠራተኞች ደመወዝ፣ ለቢሮ ኪራይ፣ ለቁጠባ ወለድ፣ ለብድር ወለድ፣ በወቅቱ ላልተመለሰ ብድር የመጠባበቂያ ወጪ፣ እንዲሁም ለሌሎች አስተዳደራዊ እና የኦፕሬሽን ተግባራት የሚውል ብር 110,547,016 ወጪ ለማድረግ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ አጠቃላይ የብር 149,240,829 ወጪ ተመዝግቧል፡፡ በመሆኑም ከተመዘገቡት ወጪዎች ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት፤ የብድር መጠባበቂያ ወጪ፣ የተቀማጭ ቁጠባ ወለድ ወጪ፣ የባንክ ብድር ወለድ ወጪ፣ የሰራተኛ ደመወዝ ወጪ፣ የኢንሹራንስ አረቦን ክፍያ ወጪ፣ የቢሮ ኪራይ ወጪ፣ እና ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች ናቸው፡፡ የበጀት ዓመቱ አጠቃላይ የወጪ መጠን ባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት ከተመዘገበው የወጪ መጠን ከብር 103,563,924 ጋር ሲነፃፀር የ45,676,905 ብር ብልጫ አለው፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በአክሲዮን ማህበሩ የተመዘገበውን የወጪ መጠን እድገት ከዚህ በታች ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

3.7 Total Expense

In the 2024/25 budget year, it was planned to spend Birr 110,547,016 for staff salaries, office rent, savings interest, loan interest, and other administrative and operational activities. The actual amount of expenses recorded until the end of the budget year was Birr 149,240,829. The accounting records show that the incurred expenses during the budget year were above the planned expenditure. In this regard, bank loan interest expense, employee salary expense, savings interest expense, cost of insurance, cost of office rent, and other administrative expenses have taken the largest portion of expenses in that order. Compared to the expenditure of Birr 103,563,924 during the last budget year, the total expenditure of the budget year showed an increase of Birr 45,676,905.

The growth of expense amount during the last five years is presented in Graph 8 below.

ምስል 9፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የወጪ መጠን

3.8 ትርፍ/ኪሳራ

ኩባንያው ባለፈው የበጀት ዓመት ከተፈጠረው ችግር ለመውጣት ባደረገው ከፍተኛ ርብርብ ተስፋ ሰጪ ወደሆነ አፈፃፀም የተመለሰ መሆኑን ከሪፖርቱ ላይ መመልከት ይቻላል።

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ ለማትረፍ የታቀደው የትርፍ መጠን ብር 71,143,750 ቢሆንም የዓመቱ አፈፃፀም ሲታይ የብር 22,111,522 ትርፍ ማስመዝገብ ተችሏል። ይህም በበጀት ዓመት ውስጥ ከታቀደው ጋር ሲነፃፀር ማሳካት የተቻለው በ31% ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ በጀት ዓመት የተመዘገበው ትርፍ ሲታይ ባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት ከተመዘገበው ኪሳራ ከብር 23,405,559 ሲነፃፀር የተገኘው ውጤት እጅግ አበረታች ነው ብለን እንወስዳለን፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ ያስመዘገበውን ትርፍና ኪሳራ ከዚህ ቀጥሎ ከቀረበው ምስል ላይ መመልከት ይቻላል።

ምስል 10፡ በአምስት ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው የትርፍና ኪሳራ መጠን

3.8 Total Profit

The profit/loss performance of the institution during the past five years is shown in Graph below.

It can be seen from the report that the company has returned to a promising performance due to the high level of efforts it made to get out of the problems that occurred in the last financial year.

Therefore, the total profit planned for the fiscal year is 71,143,750 Birr, and when the performance of the year is seen, it has registered a profit of 22,111,522 Birr. This has been achieved by 31% compared to the target in the fiscal year. Therefore, we consider that the profit recorded in this fiscal year is very encouraging compared to the loss recorded in the previous fiscal year of 23,405,559.

The profit/loss performance of the institution during the past five years is shown in Graph below.

ምዕራፍ አራት

4. የሰው ኃይልና የሌሎች ተግባሮች አፈጻጸም

4.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ

የአክሲዮን ማኅበሩን የኦፕሬሽንና አስተዳደራዊ የስራ እንቅስቃሴዎችን በተገቢው መንገድ ለማሳለጥ በተቋሙ ውስጥ ያለውንና አዲስ የሚቀጠረውን የሰው ሃይል በልምድና በክህሎት እንዲሁም በብዛትም ለማሳደግ ሁልጊዜ ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡ ስለሆነም በበጀት ዓመቱ ያሉን ቋሚና ጊዜያዊ የሰራተኞች ብዛት በዋና መ/ቤት 30፤ በዲስትሪክት 5 እንዲሁም በቅርንጫፎች 144 በድምሩ 179 ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ በቁጥር 113 ለሚሆኑ ለተቋሙ ሰራተኞችና የቦርድ አባላት የተለያዩ ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን፤ በዚሁ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በድምሩ 26 ሰራተኞች በተለያዩ ምክንያቶች ተቋሙን ለቀዋል።

4.2 የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አፈፃፀም

በተጠናቀቀው የ2017 በጀት ዓመት ከመቼውም በበለጠ የተቋሙን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የመረጃ አያያዝ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ትክክለኛና ወቅታዊ የሆነ መረጃዎችን ከኮር ባንኪንግ ሲስተም ለማግኘት ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል፡፡ ስለሆነም የተቋሙን የኦፕሬሽንና የፋይናንስ ስራዎችን ሙሉ በሙሉ በኮር ባንኪንግ ሲስተም በማስተሳሰር የሁሉንም ቅርንጫፎችና የዋና መ/ቤት መረጃ በሲስተሙ እየተሰራ የሚገኝ በመሆኑ የተሟላ መረጃ በቀጥታ ከኮር ባንኪንግ ሲስተም እንዲገኝ ተደርጓል፡፡ ይህ ተግባር በአንዴ ተሰርቶ የሚቆም ባለመሆኑ የኩባንያውን ስራ አሁን ካለው አሰራር በበለጠ ዘመናዊነቱን በጠበቀ መልኩ በዲጅታል የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽ ለማደረግ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ የውስጥ ኦፐሬሽን ስራዎችን ለማዘመንና ለማሳለጥ የሚረዱ በሲስተም የታገዙ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ። በዚሁ መሰረት በበጅት ዓመቱ ውስጥ ካቻ ከተባለው የድጅታል ኩባንያ ጋር በመሆን የድጅታል ብድርና ቁጠባ አገልግሎት መስጠት የተጀመረ በመሆኑ ደንበኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛሉ።

Chapter four

4.HR and Other Activities

4.1 Human Resource

Efforts are constantly made to grow the number of human resources in the organization by ensuring that the recently employed ones have sufficient experience and possess the fundamental skills and knowledge in order to support the operational and administrative operations of the business in an appropriate manner. As a result, the company had 30 permanent and temporary staff at the head office, 144 at the branches, and 5 at the District during the concluded fiscal year. This brings the overall number of workers at the company to 179. Compared to the total staff 188 in the previous budget year, there is a decrease by 9 staff.

4.2 Information Technology

The institution's information technology and information management system was supported by modern technology, and a lot of work was done to get accurate and up-to-date information from the core banking system. Therefore, by linking the institution's operational and financial activities with the core banking system, the information of all the branches and the head office have fully processed by the system, and a complete information is directly available from the core banking system.

As this task will not be done once and stopped, the company's work is being worked on to make digital financial services accessible in a more modern way than the current system. In addition to this, system-assisted operations are underway to modernize and streamline various internal operations. According to this, digital loan and savings services have been started in collaboration with a digital company called Kacha, and customers are also benefiting from the service.

4.3 ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የአጋርነት ትስስር ስለመፍጠር

አነስተኛ የፋይናንስ ስራ በባህሪው ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስገድድ በመሆኑ አክሲዮን ማህበሩ ከተለያዩ ባንኮች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አጋርነት በመፍጠር በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ የአጋሮቻችንን ዝርዝር ከዚህ መጽሔት መጨረሻ ገጽ ላይ መመልከት ይቻላል።

4.4 ለዳይሮክተሮች ቦርድ እና ለዋና ስራ አስፈፃሚ የተደረጉ ክፍያዎች

ለእያንዳንዱ የቦርድ አባል እና ለዋና ስራ አስፈፃሚው የተከፈለ አጠቃላይ የድካም ዋጋ፣ የአይነት ጥቅም፣ የተሰጠ ብድር ወይም የተገባ ዋስትና ካለ ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ በሚቀርበው ሪፖርት ውስጥ መካተት እንዳለበት አዲሱ የንግድ ህግ አንቀፅ 314 ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በ2017 በጀት ዓመት ለእያንዳንዱ የቦርድ አባልና ለዋና ስራ አስፈፃሚው የተደረገላቸው የአይነት ጥቅም፣ የተሰጠ ብድር እና የተገባላቸው ዋስትና ባይኖርም የተከፈላቸው የድካም ዋጋ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1፡ በ2017 በጀት ዓመት ላይ ለዳይሬክተሮችና ለዋና ስራ አስፈፃሚ የተደረጉ ክፍያዎች

4.3 Strategic Partnerships

interests.

By its nature, microfinancing business requires partnering with many stakeholders. Accordingly, Dynamic Microfinance has been working with various public and private companies including banks, and governmental and non-governmental organizations by creating business partnerships based on maintaining mutual benefits and interests.

4.4 Remunerations to the Board of Directors and Chief Executive Officer

As for the remuneration of the Board and the CEO, Article 314 of the new Commercial Code of Ethiopia stipulates that the total remuneration paid to each board member and the CEO must be included in the report submitted to the annual general meeting, if any. Accordingly, during the budget year of 2024/25, there is no payments made in-kind, loans, and guarantees which were paid to each board member. However, the remuneration paid by cash is presented in the Table below.

ተ.ቁ.	ሙሉ ስም	ኃላፊነት	የድካም ዋጋ		የአይነት ጥቅም	የተሰጠ ብድር	የተገባ ዋስትና
			በወር	በአመት	በአመት	በአመት	በአመት
1	አቶ ተስፋዬ ፈንቴ	ሰብሳቢ	-	120,000	-	-	-
2	አቶ በቀለ ባይሳ	ም/ሰብሳቢ	-	96,000	-	-	-
3	አቶ አበባው ዘውዴ	አባል	-	96,000	-	-	-
4	አቶ ወርቅነህ ተስፋዬ	አባል	-	96,000	-	-	-
5	አቶ መንገሻ ዲበኩሉ	አባል	-	96,000	-	-	-
6	አቶ ብናልፈው ነጋ	አባል	-	96,000	-	-	-
7	አቶ ሳሙኤል ታደሰ	አባል	-	96,000	-	-	-
8	አቶ ይልማ ገብሬ	አባል	-	96,000	-	-	-
9	አቶ ዮሐንስ እምሩ	አባል	-	96,000	-	-	-
10	አቶ በዕውቀቱ አላምረው	ዋና ስ/አስፈፃሚ	107,000	-	-	-	-

4.5 ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ዋና ዋና ተግባሮች

በበጀት ዓመቱ በስራ አፈፃፀም ወቅት እንደቁልፍ ተግባር የተወሰዱና ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ዋና ዋና ተግባሮች:

- የተበላሸ ብድር ለማስከፈል ከፍተኛ የሆነ ርብርብ ማድረግ፣
- የኩባንያውን የካፒታል መጠን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ፣
- የቆጣቢዎችና የተበዳሪዎችን ቁጥር ማሳደግ፣
- ያሉንን ሁሉንም ቅርንጫፎች ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ ማስቻል፣
- ወጪ ቆጣቢ የሆነ ስራ የመስራት ባህልን ማዳበር፣
- ህጋዊነት ያለው አሰራር በመከተል ተግባሮችን በህግና ስርዓት ማከናወን የሚሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

4.6 ለቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራባቸው ነጥቦች

በቀጣይ በ2018 በጀት ዓመት የሁሉንም የተቀናጀ ጥረት የሚሹ የሚከተሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት ከፍተኛ ክትትል እየተደረገባቸዉ የሚከናወኑ ይሆናል።

1) የሀብት ማሰባሰብ እና አጠቃቀም ላይ ጠንካራ ስራ መስራት፤
2) ለፋይናንስ ጤናማነት ዘላቂ ትርፋማነትን ማረጋገጥ፤
3) የማርኬቲንግ እና የማስተዋወቂያ ስራዎችን ማጠናከር፤
4) የተለያዩ የስራ ሂደቶችን ማዘመንና በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ፤
5) የብድር ጥራትን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፤
6) የሰው ኃይል ልማት ላይ ጠንካራ ስራ መስራት፤
7) የውስጥ ቁጥጥርን ማጠናከር፤
8) የስጋት አስተዳደር እና ለህግና ለመመርያ ተገዢነት ላይ የማያወላዳ ስራ መስራት ናቸው።

4.5 Key Improvement Areas

During the plan period under review, DMFI has identified areas that require further improvements to achieve its targets and enhance overall performance. The key areas that require attention and action include:

- Putting a more aggressive effort into the loan recovery activity.
- Enhancing the subscribed and paid-up capital to face the challenges related to capital limitations.
- Increase Customer Base and Deposit Mobilization.
- Increase branches' productivity and efficiency.
- Enhance staff engagement and productivity.
- Encouraging and fostering a cost-conscious culture.
- Insure the compliance issues with directives and laws.

4.6 Major Focus Areas for the Next Plan Period

The following core areas are identified as major focus areas that need the concerted effort of all during the next budget year 2025/26.

1) Focusing on resource mobilization and resource allocation;
2) Maintaining financial soundness and sustainability;
3) Focusing on marketing and promotional activities;
4) Strengthening internal business processes;
5) Maintaining portfolio quality;
6) Strengthening the human resource development;
7) Focusing on the CBS transformation and modernization;
8) Ensuring risk management and compliance engagements.

4.7 ማጠቃለያ

ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ተቋማችን ከምን ጊዜውም በላይ የተፈተነበት ወቅት ሆኖ አልፏል። ሆኖም ያጋጠሙ ችግሮችን ሁሉ ተቋቁሞ ስራውን ለማስቀጠል እና የኩባንያውን ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ቦርዱና ማኔጅመንቱ የተለያዩ ስልቶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚሁ መሰረት ኩባንያው ከደንበኞች ጋር ያለው ግንኙነት ችግር ሳይፈጠር እንዲቀጥል ለማድረግ ቁጣባ የማሰባሰብ ስራ ላይ ልዩ ትኩራት በማድረግ፤ የባንኮች ብድር በወቅቱ እዲከፈልና እንዲሁም ደንበኞች በፈለጉት ጊዜ የቁጠባ ወጪ ማድረግ እንዲችሉ በማድረግ ረገድ ጠንካራ ስራ ተስርቷል። እንዲሁም የቁጥጥርና የክትትል ስራው ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እንዲጠናከር በማድረግና ከቅርንጫፎች ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የሰላም ችግር ካለባቸው አካባቢዎችም ቢሆን በርካታ ብድሮችን የማስመለስ ስራ ተሰርቷል።

ከዚህ በተጨማሪም ሰላም ባለበት በአዲስ አበባና በኦሮሚያ አካባቢ ያሉን ቅርንጫፎች ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው እንዲሰሩ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ከዚህ በፊት ከነበረው በላይ በብድርና ቁጠባ ስራ ላይ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ተደርጓል።

ስለሆነም ኩባንያችን በቀጣይ የበጀት ዓመት ከዚህ የላቀ አፈፃፀም እንዲያስመዘግብ የሥራ አመራሩና የሠራተኛው ጥረት የበለጠ ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን ከባለአክሲዮኖችም ከዚህ በፊት ከነበረው የበለጠ ትብብር ስለሚያስልግ ሁላችንም በምንችለው አቅም ሁሉ በኩባንያው ቁጠባ እንድንቆጥብና የተመደበልንን አክሲዮን በመግዛት ኩባንያውን እንድናግዝ ቦርዱ በአክብሮት ጥሪውን በድጋሜ ያቀርባል፡፡

4.7 Conclusion

The concluded financial year has tested Dynamic Microfinance Institution like never before. The board and the management have been preparing and implementing various strategies to overcome the problems encountered in the institution in connection with various internal and external issues as and when they materialize in the fiscal year.

As a result, despite the challenges faced, the company's relationship with its stakeholders continues without problems, with a special focus on the mobilization of resources, ensuring that bank loans are repaid on time, and customers can withdraw their savings whenever they want. Also, by strengthening the control and monitoring work and strengthening the follow-up relationship with branches, encouraging loan recovery work has also been done in areas with peace and security problems.

Moreover, uninterrupted follow-up and support were also being given to branches in Addis Ababa and the Oromia region, so that they could perform to their fullest potential and achieve better results in credit and savings than before.

We would also like to assure you that the board, management, and employees will continue strengthening their efforts while also seeking more support, cooperation, and understanding from the shareholders than ever before. In view of this, the Board respectfully invites all shareholders to participate in the company's resource mobilization activities and most importantly fulfill commitments with the allotted shares to respective shareholders to the best of their abilities and in turn benefit from the fruitful results.

በመጨረሻም አክሲዮን ማኅበሩ በሚያከናውናቸው ተግባሮች ሁሉ ድጋፍና እገዛ ስታደርጉልን ለነበራችሁ ባለአክሲዮኖች፣ ጠንክራችሁ ስትሠሩ ለነበራችሁ የማኔጅመንት አባላት እና ሠራተኞች፣ በኩባንያው ገንዘብ ያስቀመጣችሁ ደንበኞች፣ እንዲሁም ምንጊዜም ያልተቆጠበ ድጋፍና ክትትል ለሚያደርግልን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ለሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ እና ለሌሎች ተባባሪ አካላት ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና እያቀረብን በ2018 በጀት ዓመት ሀገራችን ውስጥ በሁሉም አካባቢ ሰላም ሰፍኖ ጠንካራና ፅኑ መሰረት ያለው ኩባንያ ለመገንባት የያዝነውን ራዕይ ለማሳካት አቅም የምንፈጥርበት ዘመን እንዲሆንልን የዳይሬክተሮች ቦርድ መልካም ምኞቱን ይገልጻል፡፡

ፈጣሪ አገራችንና ህዝባችንን ይባርክ!

አመሰግናለሁ!

ተስፋዬ ፈንቴ

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር

ታህሳስ 4 ቀን 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

Finally, we would like to express our sincere gratitude to the shareholders who have been supporting and helping us in all the activities of the company, to the management members and employees who have been working hard, as well as to the National Bank of Ethiopia, the Document Authentication and Registration Agency and all other partners. The Board of Directors expresses its best wishes for the 2025/26 fiscal year to be a time of peace in our country where we restore the sustainability and growth of our institution.

May God bless our country and its people.

Thank you!

Tesfaye Fente

Chairman, Board of Directors

December 13, 2025

Addis Ababa

Strategic Partners/ አጋሮቻችን

Dynamic in Pictures

Dynamic in Pictures

ቅርንጫፎቻችን / Our Branches

ተ. ቁ. No.	የቅርንጫፍ ስም BRANCH NAME	ስልክ PHONE	ከተማ CITY	መገኛ አድራሻ LOCATION
1	ኡራኤል / Urael	0115579472	አዲስ አበባ	ሸገር ህንፃ፣ 1ኛ ፎቅ
2	ዱከም / Dukem	0114718472	ዱከም	ቲ ዜድ የገበያ ማዕከል፣ 2ኛ ፎቅ
3	ውጫሌ / Wuchale	0111340714	ሙከጡሪ	ሲራጅ ህንፃ (አዋሽ ባንክ)
4	ቃሊቲ / Kality	0114715783	አዲስ አበባ	ወይንሸት ደመና ህንፃ፣ 2ኛ ፎቅ
5	አዳማ / Adama	0228110906	አዳማ	አዋሽ ባንክ ህንፃ፣ 1ኛ ፎቅ
6	ሰንዳፋ / Sendafa	0116387282	ሰንዳፋ	መ/ኃይል ፊት ለፊት ፥ 1ኛ ፎቅ
7	ጉለሌ / Gullele	0111547298	አዲስ አበባ	ሸገር ግራንድ ሞል
8	የካ / Yeka	0116733711	አዲስ አበባ	ንጉሥ ህንፃ፣ 2ኛ ፎቅ (02)
9	ገርጂ / Gerji	0116394613	አዲስ አበባ	አትክልትና ፍራፍሬ ገበያ ማዕከል፣ 2ኛ ፎቅ
10	ጀሞ / Jemo	0113699916	አዲስ አበባ	ፒዮኒ ኮሜርሻል፥ 3ኛ ፎቅ
11	ቸርችል / Churchill	0111719111	አዲስ አበባ	ልደታ ዋና መ/ቤት ህንፃ፣ 3ኛ ፎቅ
12	ሞጣ / Mota	0586612025	ሞጣ	አቶ አያሌው ህንፃ
13	ሉማሜ / Lumame	0587720670	ሉማሜ	አቢሲኒያ ባንክ አጠገብ
14	ዳንግላ / Dangila	0582211818	ዳንግላ	አገው ምድር አዳራሽ ፊት ለፊት
15	ቲሊሊ / Tilili	0582290686	ቲሊሊ	አድማስ ህንፃ
16	ቡሬ / Bure	0587741745	ቡሬ	አባ ካሳዬ ህንፃ
17	ደ/ማርቆስ / D/Markos	0581780998	ደ/ማርቆስ	አዲስ ህንፃ
18	ቢቸና / Bichena	0586651672	ቢቸና	ንጉሥ ይግዛው ህንፃ
19	ደ/ወርቅ / D/Work	0586630672	ደ/ወርቅ	አንተነህ መንግስቱ ህንፃ
20	ባ/ዳር ቅ/ፍ / B/Dar Br.	0583203738	ባ/ዳር	መስራት ያስከብራል የገበያ ማዕከል
21	ፍ/ሰላም / F/Selam	0587753100	ፍ/ሰላም	ቡና ባንክ ፊት ለፊት
22	እንጅባራ / Injibara	0582271192	እንጅባራ	አርዲዳን ህንፃ
23	ወረታ / Woreta	0584461174	ወረታ	ዓለም ፔንሲዮን
24	ሰከላ / Sekela	0582590636	ሰከላ	
25	ግምጃቤት / Gimjabet	0948780114	ግምጃቤት	
26	አዘና / Azena	0936894044	አዘና	
27	ቻግኒ / Chagni	0943446553	ቻግኒ	
28	ሸንዲ / Shindi	0980281805	ሸንዲ	
29	ባ/ዳር ዲስትሪክት / B/Dar District	0920287835	ባ/ዳር	መስራት ያስከብራል የገበያ ማዕከል

የዋና መስሪያ ቤት አድራሻ

HEAD OFFICE ADDRESS

አዲስ አበባ ልደታ፣ ወረዳ 09 ባልቻ ሆስፒታል አፍ ብሎ

Addis Ababa, Lidetta, Woreda 09, Near Balcha Hospital

ስልክ/ Tel.: +251 115 156 817/ +251 115 579 632

ፋክስ/ Fax: +251 115 157 090 ፓ.ሳ.ቁ/ P.O.Box:20943/1000

ኢሜል/E-mail: info@dynamicmfi.com/
dynamicmfisc@gmail.com

ዌብሳይት/ Website: www.dynamicmfi.com